## የኢትዮጵያ ምርት ገበያ የወስጥ ደንብ ማሻሻያ ቁጥር 559/2013

### 1. መግቢያ

1.1 የተሻሻለዉን የኢትዮጵያ ምርት ገበያ የወስጥ ደንብ ቁጥር 12/2012ን (ከዚህበኋላ "ደንብ" በመባል ይጠቀሳል) ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በማኘቱ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ (ከዚህበኋላ "የምርትገበያ" በመባል ይጠቀሳል) በምርት ገበያዉ ማቋቋሚያ አዋጅቁጥር 775/1999 አንቀጽ 12(10) መሠረት ይህንን የወስጥ ደንብ ማሻሻያ አወጥቷል፡፡

1.2 ይህን የወስጥ ደንብ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን (ከዚህበኋላ "ባለሥልጣን" ተብሎይጠቀሳል) በባለሥልጣኑ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 551/1999 አንቀጽ 6(3) በተሰጠዉ ስልጣን መሠረት ካፀደቀዉ በኋላ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

1.3 ይህየወስጥ ደንብ "የኢትዮጵያ ምርት ገበያ የወስጥ ደንብ ማሻሻያ ቁጥር "775/2013" በመባል ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ማሻሻያ

የተሻሻለዉ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ **የወስጥ** ደንብ ቁጥር **559/2013** (ከዚህበኋላ"ደንብ"ተብሎ ሊጠቀስይችላል) እንደሚከተለዉ እንደገና ተሻሽሏል፡፡

(1) የሚከተለዉ አዲስ ንኡስ አንቀጽ 4.1.8 በደንቡ አንቀጽ 4.1 ስር ተጨምሯል፡፡የደንቡ ንዑስአንቀፅ 4.1.8የነበረወንዑስአንቀፅ 4.1.9ሆኖተሸጋሽጓል፡፡

"4.1.8 የምርት ገበያወን ዝርዝር መመሪያ ማነረት በማድረግ በተመሳሳይ የአባልነት መደብ ወስጥ ወደሚገኝ ሌላ የአባልነት መደብ መቀየር ወይም ማለወጥእንዲሁም ከአባልነት መደብ ወደ አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይነት መደብ መቀየር ወይም ማለወጥ ይቻላል፡፡ ሆኖም ግን ከልዩ አባልነት መደብወደ መደበኛ አባል ወይም ከመደበኛ አባል ወደ ልዩ አባልነት መደብእንዲሁም ከአባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይነት መደብ ወደ አባልነት መደብ መቀየር አይቻልም፡፡"

(2) የሚከተለዉ አዲስ ንኡስ አንቀጽ 4.2.5 በደንቡ አንቀጽ 4.2 ስርተጨምሯል፡፡የደንቡ ንዑስ አንቀፅ 4.2.5 የነበረው ንዑስ አንቀፅ 4.2.6 ሆኖ ተሸጋሽጓል፡፡

"4.2.5 ከላይ በንዑስ አንቀፅ 4.2.2፣ 4.2.3 እና 4.2.4 የተደነገገው ቢኖርም፣በምርት ገበያው በአባልነት ወይም አባል ባልሆነ ቀጥታ ተገበያይነት እየሰራ ባለድርጅት ወስጥ የባለቤትነት ድርሻ ቢኖራቸወም በልዩ የግብይት ማከኮት አባል ባልሆነ ቀጥታ ተገበያይነት እንዲስተናገዱ በደንቡ በንኡስ አንቀጽ 4.17.1.8 ማነረት ሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ያለው ተቋም በሚልከው የተገበያዮች ዝርዝር ወስጥ የተካተቱ ግለሰቦች እና ድርጅቶች በልዩ የግብይት ማከኮት አባል ባልሆነ ቀጥታ ተገበያይነት እንዲሳተፉ ሊፈቀድላቸው ይችላል፡፡

(3) የሚከተለዉ አዲስ ንኡስ አንቀጽ 4.7.1.9 በደንቡ ንኡስ አንቀጽ 4.7.1 ስር ተጨምሯል፡፡ ከደንቡ ንዑስ አንቀፅ 4.7.1.9 እስከ 4.7.1.14 ያሉት ከንዑስ አንቀፅ 4.7.1.10 እስከ 4.7.1.15 ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡

"4.7.1.9 አባሉ ከተፈቀደለት የተገበያይነት መደብ ወይም አይነት ወጪ እና እንዲገበያይ ከተፈቀደለት የግብይት ማእከል ወይም ቦታ ወጪ ግብይት ፈጽሞ ከተገኘ"

(4) የሚከተለዉ አዲስ ንኡስ አንቀጽ 4.7.2.1 (ረ) በደንቡ ንኡስ አንቀጽ 4.7.2.1 ስር ተጨምሯል፡፡ ከደንቡ ንዑስ አንቀፅ 4.7.2.1 (ረ) እስከ (ሰ) ያሉት ከንዑስ አንቀፅ 4.7.2.1 (ሰ) እስከ (ሸ) ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡

"4.7.2.1 (ረ) የደንበኛን የሽያጭ ወይም የግዥ ትእዛዝ በትክክል መዝግቦ ካልያዘ፣ ቅደም ተከተሉን ካዛባ እንዲሁም በደንበኛ የተሰጠዉን የግብይት ትእዛዝ በአግባቡና በጊዜው ካልፈጸመ"

(5) የደንቡ ንኡስ አንቀጽ 4.8.6 እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"4.8.6 በዚህ አንቀጽ የተመለከተው ሥነ ሥርዐት፤

ሀ. በአንድ ድርጅት ሥር ባሉ ተቀጥያ ድርጅቶች መካከል በሚደረግ ማስተላለፍ፣

ለ. የሽርክና ማኅበር ከሆነ፣ለማኅበሩ ሽሪክ ወይም ከ50 በመቶ በላይ ድርሻ በሽሪኩ ባለቤትነት ለተያዘ ድርጅት፣

ሐ. ግለሰብ አባል የሆነ ከሆነ፣ግለሰቡከ50 በመቶ በላይ የአክሲዮን ድርሻ ለያዘበት ድርጅት ወይም

መ. የህብረት ስራ ማህበር ከሆነ፣ማህበሩ አባል በሆነበት ሌላ የህብረት ስራ ማህበር የሚደረግ ማስተላለፍ፤ላይ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡"

(6) የሚከተለዉ አዲስ ንኡስ አንቀጽ 4.8.7 በደንቡ ንኡስ አንቀጽ 4.8 ስር ተጨምሯል፡፡ ከደንቡ ንዑስ አንቀፅ 4.8.7 እስከ 4.8.9 ያሉት ከንዑስ አንቀፅ 4.8.8 እስከ 4.8.10 ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡

"4.8.7 በአንቀፅ4.8.6 መሰረት የአባልነትመቀመጫ የሚያስተላልፍ አባል ለምርት ገበያው የአገልግሎት ክፍያ ይከፍላል፡፡ በባለስልጣኑ መፅደቅ እንደተጠበቀ ሆኖ የዚህ ክፍያ መጠን በምርት ገበያው ቦርድ ይወሰናል፡፡"

(7) የሚከተለዉ አዲስ ንኡስ አንቀጽ 4.10.1.5 በደንቡ ንኡስ አንቀጽ 4.10.1 ስር ተጨምሯል፡፡

"4.10.1.5 ማንኛውም የግብይት ተወካይ ከወከለው አባ ለቅቆ ወደ ሌላ አባል ወይም አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይ ለመቀየር መብት ያለው ቢሆንም ቀድሞ ለወከለው አባል ቢያንስ ለአንድ ዓመት ያህል አገልግሎት

ያልሰጠ ከሆነ ግን ወደ ሌላ አባል ወይም አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይ ለመቀየር እና የግብይት ተወካይ ሆኖ ለማገልገል ቀድሞ ከተወከለበት አባል ከለቀቀ ጊዜ አንስቶ ቢያንስ አንድ አመት መቆየት ይኖርበታል፡፡ ሆኖም የአባሉ እወቅና ቢያንስ ለሶስት ወራት ታግዶ ከቆየ፣ እወቅናው ከተሰረዘ፣ የአባልነት መቀመጫውን ለሌላ ሰው ካስተላለፈ፣ ድርጅቱ በህግ ማስረት ከፈረሰ፣ ለምርት ገበያው በቀጥታ በተፃፈ ደብዳቤ የግብይት ወኪሉን በፈቃዱ ያሰናበተው መሆኑን ከገለፀ ወይም የገበያውን ደህንነት ለማጠበቅ ሲባል በምርት ገበያው በልዩ ሁኔታ ከተፈቀደለት ከዚህ በላይ የተመለከተው የአንድ ዓመት አገልግሎትና የቆይታ ጊዜ በግብይት ወኪሉ ላይ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡"

(8) የሚከተለዉ አዲስ ንኡስ አንቀጽ 4.12.6 በደንቡ ንኡስ አንቀጽ 4.12 ስር ተጨምሯል፡፡

"4.12.6 አባሉ በምርት ገበያው ለማበያት የሚያቀርባቸው ሰነዶች ትክክለኛ ስለመሆናቸው ተገቢውን ማጣሪያ የማድረግ እንዲሁም ወደ ግብይት ከመግባቱ በፊት በምርት ገበያው የተመዘገበው መረጃ ትክክለኛ መሆኑን የማጣራት ኃላፊነት አለበት፡፡ በአባሉ የሚቀርቡ የብቁነት ሰነዶች በኤሌክትሮኒክ መንገድ ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡ በምርት ገበያው በማንኛውም ጊዜ ሰነዶችን ለምርመራ እንዲያቀርብ ሲጠየቅ የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡"

(9) የሚከተለዉ አዲስ ንኡስ አንቀጽ 4.17.1.2 በደንቡ ንኡስ አንቀጽ 4.17.1 ስር ተጨምሯል፡፡ ከደንቡ ንዑስ አንቀፅ 4.17.1.2 እስከ 4.17.1.3 ያሉት ከንዑስ አንቀፅ 4.17.1.3 እስከ 4.17.1.4 ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡

"4.17.1.2 በቦርዱ በሚወሰነው መስረት ማንኛውም ሰው አንድ ምርት ወይም የተወሰኑ ምርቶችን ብቻ ለማበያየት በምርት ገበያው በግብይት እንዲሳተፍ አባል ባልሆነ ቀጥታ ተገበያይነት ሊፈቀድለት ይችላል፡፡"

(10) የሚከተሉት አዲስ ንኡስ አንቀጾች 4.17.1.5፣ 4.17.1.6፣ 4.17.1.7፣4.17.1.8 እና 4.17.1.9 በደንቡ ንኡስ አንቀጽ 4.17.1 ስር ተጨምረዋል፡፡ የደንቡ ንዑስአንቀፅ 4.17.1.4የነበረውንዑስአንቀፅ 4.17.1.10ሆኖተሸጋሽጓል፡፡

"4.17.1.5 ማንኛውም በንኡስ አንቀጽ 4.17.1.2 መስረት በምርት ገበያው አንድ ምርት ወይም የተወሰኑ ምርቶችን ብቻ ለማበያየት በምርት ገበያው በግብይት እንዲሳተፍ የተፈቀደለት አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይ እንዲገበያይ የተፈቀደለትን ምርት ወይም ምርቶች ብቻ በምርት ገበያው ለማበያየት የተስማማ መሆኑን በምርት ገበያው የተዘጋጀ ቅጽ በመሙላት በፊርማው በማረጋገጥ ግዴታ መግባት ይኖርበታል፡፡

4.17.1.6 ማንኛውም በንኡስ አንቀጽ 4.17.1.2 መስረት በምርት ገበያው አንድ ምርት ወይም የተወሰኑ ምርቶችን ብቻ ለማበያየት በምርት ገበያው በግብይት እንዲሳተፍ የተፈቀደለት አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይ እንዲገበያይ ከተፈቀደለትን ምርት ወይም ምርቶች ወጪ ባሉ ምርቶች ግብይቶች ላይ ለመሳተፍ የሚችለው በንኡስ አንቀጽ 4.17.1.5 ላይ የተገለጸውን የግዴታ መግቢያ

ሰነድ በማቋረጥ እንዲሁም ለማበያየት ከተፈቀደለት ምርት ወይም ምርቶች ወጪ ባሉ ምርቶች ግብይቶች ላይ ለማካተፍ የሚያስችለወን የመገቢያ ማስፈርቶች እና ቅድመ ሁኔታዎች ያሟላ እና የምርት ገበያወን ፍቃድ ያገኘ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡

4.17.1.7 በተለያየ አይነት አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይ መደብ ወስጥ የሚገኝ ሰው የምርት ገበያወን ዝርዝር መመሪያ ማስረት በማድረግ በሻጭ ወገን ወደሚገኝ አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይ መደብ ለመቀየር ወይም ለማስወጥ ይችላል፡፡

4.17.1.8 በምርትገበያወበአባልባልሆነቀጥታተገበያይነትመደብበንኡስ አንቀጽ 4.17.1.2 ማስረት እንዲሳተፉ የተፈቀደላቸወን ተገበያዮች ዝርዝር፣የሚገዙትን ምርት ማጠን እና የግብይት ፈቃዱ የሚያገለግልበትን የጊዜ ገደብ ሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ያለው ተቋም ለምርት ገበያው ሲያሳወቅ ምርት ገበያው ይህንኑ ማስረት በማድረግ ተገበያዮችን ይቀበላል፡፡

4.17.1.9 በምርት ገበያው መቀመጫ ያላቸው አባላት እና አባል ባልሆነ ቀጥታ ተገበያይነት በግብይት እየተሳተፉ የሚገኙ ሰዎች ከላይ በንኡስ አንቀጽ 4.17.1.8 ስር በተጠቀሰው ዝርዝር ወስጥ ተካተው ከተገኙ በተጠቀሰው ልዩ ግብይት እንዲሳተፉ ሊደረግይ ችላል፡፡"

(11) የሚከተለዉ አዲስ ንኡስ አንቀጽ 4.17.11.1.5 በደንቡ ንኡስ አንቀጽ 4.17.11.1 ስር ተጨምሯል፡፡

"4.17.11.1.5 ማንኛወም የግብይት ተወካይ ከወከለው አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይ ለቅቆ ወደ ሌላ አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይ ወይም አባል ለመቀየር መብት ያለው ቢሆንም ቀድሞ ለወከለው አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይ ቢያንስ ለአንድ አመት ያህል አገልግሎት ያልሰጠ ከሆነ ግን ወደ ሌላ አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይ ወይም አባል ለመቀየር እና የግብይት ተወካይ ሆኖ ለማገልገል ቀድሞ ከተወከለበት አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይ ከለቀቀ ጊዜ አንስቶ ቢያንስ አንድ ዓመት መቆየት ይኖርበታል፡፡ ሆኖም አባል ያልሆነው ቀጥታ ተገበያይ እወቅናው ቢያንስ ለሶስት ወራት ታግዶ ከቆየ፣ እወቅናው ከተሰረዘ፣ የተገበያይነት መብቱን ካቋረጠ፣ ድርጅቱ በህግ ማስረት ከፈረሰ፣ ለምርት ገበያው በቀጥታ በተፃፈ ደብዳቤ የግብይት ወኪሉን በፈቃዱ ያሰናበተው መሆኑን ከገለፀ ወይም የገበያወን ደህንነት ለማጠበቅ ሲባል በምርት ገበያው በልዩ ሁኔታ ታይቶ ከተፈቀደለት ከዚህ በላይ የተማከተው የአንድ ዓመት አገልግሎትና የቆይታ ጊዜ በግብይት ወኪሉ ላይ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡"

(12)የደንቡ ንኡስ አንቀጽ 5.5.1.4 እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"5.5.1.4 የምርቱን ባለቤት ማንነት እና የምርት ዱካን ባስጠበቀ ሁኔታ ለሚደረግ ምርት ግብይት የመጀመሪያ ዋጋ በሻጭ ይሰጣል፡፡ ይህን ተከትሎ ሻጭ በሰጠው ዋጋ ላይ በመመስረት በዋጋ ገደቡ ወስጥ የመጀመሪያ የግዥ ዋጋ በገዢው ማስጠት አለበት፡፡"

(13) የሚከተለዉ አዲስ ንኡስ አንቀጽ 5.3.7 በደንቡ ንኡስ አንቀጽ 5.3 ስር ተጨምሯል፡፡

"5.3.7 በአንቀጽ 5.3.6 ላይ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ለማንኛውም ምርት ለሚደረግ ግብይት የሚታይ ቅድመ-ግብይት መረጃ የግብይት ክፍለ ጊዜ ከመካፈቱ ቢያንስ ከግማሽ ሰአት በፊት በተመሳሳይ ጊዜ ለሁሉም ለተገበያዮች ይፋ መደረግ አለበት፡፡

5.3.7.1 ድምጽንበማስተጋባት ወይም በኤሌክትሮኒክ የመገበያያ መድረክ ላይየሚደረግ ግብይትን በተመለከተ ሁሉም ቅድመ-ግብይት መረጃ በማስታወቂያ ሰሌዳ ወይም ተገቢ በሆነ ሌላመንገድ ለተገበያዮች እንዲታይ ይደረጋል፡፡

5.3.7.2 ለማንኛውም ምርት የሚደረግ ግብይትን በተመለከተ የሚታይ ቅድመ-ግብይት መረጃ ቢያንስ የሚከተሉትን ያካተተ መሆን አለበት፤

i. የምርትርክክብደረሰኝ/የማከማቻመጋዘንደረሰኝቁጥር

ii. የምርቱጥራት ደረጃ

iii. የተቀማጠበት መጋዘን ወይምቅርንጫፍ

iv የምርትዘመን

v. የምርትመለያምልክት

vi. ምርትገበያውአስፈላጊናቸውብሎያመነባቸውሌሎችመረጃዎች፡፡

5.3.7.3 የምርት ገበያው አሰራር ወይም ሲስተም አንቀጽ 5.3.7.2 ላይ የተጠቀሱትን በማካተት ለማንኛውም ምርት የሚደረግ ምርት ግብይት ወል መረጃን ማውጣት አለበት፡፡"

(14) የሚከተለዉ አዲስ ንኡስ አንቀጽ 5.4.6 በደንቡ ንኡስ አንቀጽ 5.4 ስር ተጨምሯል፡፡ የደንቡ ንዑስ አንቀፅ 5.4.6 የነበረው ንዑስ አንቀፅ 5.4.7 ሆኖ ተሸጋሽጓል፡፡

"5.4.6 በሚኒስቴሩ ወይም አግባብነትባለውተቋም የሚወጣ እለታዊ የዋጋ ገደብ

እለታዊ የዋጋ ገደብ አወሳሰንን የተመለከቱ የደንቡ ንኡስ አንቀጾች 5.4.3፣ 5.4.4 እና 5.4.5 ላይ ያሉ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የተለየ ሁኔታ ባጋጠመ ጊዜ ወይም አስፈላጊ መሆኑ ሲታመንበት ሚኒስቴሩ ወይም አግባብነትያለውተቋም በሚያወጣው እለታዊ የዋጋ ገደብ በመመስረት በምርት ገበያው የወሎች ግብይት ሊደረግ ይችላል፡፡"

(15) የደንቡ ንኡስ አንቀጽ 5.5.5 እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"5.5.5 ግብይቶች

ኤሌክትሮኒክ የግብይት መድረክ የተፈጸሙ ግብይቶችን ዝርዝር መረጃ በሙሉ ለተገበያዮች እንዲታይ ሊያደርግ ይችላል፡፡ የተከናወኑ ግብይቶች በሙሉ በተከናወኑበት ዕለት በክፍያና ርክክብ መሜያ ሥሪት ክፍያ እንዲፈፀም ለምርት ገበያው የክፍያ ሜፀሚያ ተቋም መቅረብ አለባቸው።"

(16) የደንቡ ንኡስ አንቀጽ 7.25.13.1፣ 7.25.13.2 እና 7.25.13.3 የነበሩት 7.25.14.1፣ 7.25.14.2 እና 7.25.14.3 ሆነው ተሸጋሽገው እንደሚከተለዉ ተሻሽለዋል፡፡

"7.25.14.1 የምርት ገበያው የምርት የቴክኒክ ባለሙያ የቀረበውን የወል ማሻሻያ ሀሳብ ከመረመረና በምርት ገበያው አመራር ይሁንታ ካገኘ በኋላ የወል ማሻሻያ ሃሳቡን ወድቅ ለማድረግ ወይም በንዑስ አንቀፅ 7.25.5 መሰረት ለኢንዱስትሪ ምክክር ኮሚቴ ሊመራ ይችላል::

7.25.14.2 የምርት ገበያው በንኡስ አንቀጽ 7.25.14.1 መሰረት በሰጠው ወሳኔ ቅር የተሰኘ አካል ወሳኔው በደረሰው በአስር ቀናት ወስጥ ይግባኙን ለኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን ማቅረብ ይችላል::

7.25.14.3 ባለሥልጣኑ ከላይ በንኡስ አንቀጽ 7.25.14.2 መሰረት በቀረበለት ይግባኝ የሚሰጠው ወሳኔ የመጨረሻ ይሆናል::"

(17) የደንቡ ንኡስ አንቀጽ 7.25.14 እና 7.25.14.3 የነበሩት 7.25.15 እና 7.25.15.3 ሆነው ተሸጋሽገው እንደሚከተለዉ ተሻሽለዋል፡፡

"7.25.15 የኢንዱስትሪ ምክክር ኮሚቴ በንዑስ አንቀፅ 7.25.5 መሰረት ፍላጎቱ ያለው የምርት ገበያው አባል ወይም በምርት ገበያው የቀረበለትን እና አግባብነት አለው ብሎ ያመነበትን ማናቸውንም የወል ማሻሻያ ሃሳብ ለምርት ገበያው ለማቅረብ ይችላል፡፡

7.25.15.3 ባለስልጣኑ ከላይ በንኡስ አንቀፅ 7.25.15.2 መሰረት በቀረበለት ይግባኝ የሚሰጠው ወሳኔ የመጨረሻ ይሆናል::"

(18) የደንቡ ንኡስ አንቀጽ 8.12.6 እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"8.12.6 በደንቡ አንቀጽ **8.12.5** ሥር ከተመለከቱት በተጨማሪ ማንኛወም የተከለለ ጥብቅ ማቆያ ሥፍራ የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን አለበት፡-"

(19) የሚከተለዉ አዲስ ንኡስ አንቀጽ 14.3.10 በደንቡ ንኡስ አንቀጽ 14.3 ስር ተጨምሯል፡፡

"14.3.10 አባሉ ደንበኛውን በመወከል የደንበኛውን አስፈላጊ የግብይት ብቁነት ሰነዶች ለምርት ገበያው ማቅረብ ይችላል፡፡ አባሉ የደንበኛውን ሰነድ በሚያከብ ጊዜ ስለትክክለኛነቱተገቢውን ማጣሪያ በማድረግ ለምርት ገበያው የማስረከብ እንዲሁም የደንበኛውን ትእዛዝ ከሚፈጸሙ በፊት የደንበኛው መረጃ በምርት ገበያው በትክክል መመዝገቡን የሚረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡ ሰነድ የማስረከብ ሂደት በኤሌክትሮኒክ መንገድ ሊሆን ይችላል::"

**(20)** የሚከተለዉ አዲስ ንኡስ አንቀጽ 15.3.3.4 በደንቡ ንኡስ አንቀጽ 15.3.3 ስር ተጨምሯል፡፡ የደንቡ ንዑስ አንቀፅ 15.3.3.4 የነበረው ንዑስ አንቀፅ 15.3.3.5 ሆኖ ተሸጋሽጓል፡፡

"15.3.3.4 በተከታታይ ስድስት ወራት ወስጥ ሶስት እና ከዚያ በላይ የዲሲፐሊን ጥፋቶችን የፈጸመ የግብይት ወኪል እንደጥፋቱ ክብደት እና አይነት ከምርት ገበያ የግብይት መድረክ እስከ አንድ አመት የሚደርስ እገዳ ሊጣልበት ይችላል፡፡"

3. **ተፈጻሚ የሚሆንበት ቀን**

በደንቡ ንዑስ አንቀጽ 21 (1) መሰረት ይህ ደንብ በባለሥልጣኑ ከጸደቀ ከአስራ አራተኛው ቀን በ|ላ ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

**በኢትዮጵያ ምርትገበያ ባለሥልጣን ቦርድ መስከረም 11 ቀን 2013 ዓ.ም**

**በአዲስ አበባ ጸደቀ፡፡**